# በአካል በመገኘት ግምገማና ቀጠሮ

በ Early Stages (DCPS) በመጀመርያ ደረጃ ፣ የቤተሰቦች ጤና እና ደህንነት እንደ ተቀዳሚ ተግባራችን ሆነው ይቀጥላሉ። ድርጊቶቻችን የ DC ጤና እና የስቴቱ የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ መመርያን የተከተለ ነዉ።

*ለቀጠሮ መዘጋጀት*

ከቀጠሮዉ ቀደም ብሎ በመጀመርያ ደረጃ፤

- በቀጠሮዉ ላይ 1 አዋቂ ሰዉና 1 ልጅ ብቻ እንድገኙ እንደሚፈቀድ ልብ ይበሉ።
- እርስዎ እና ልጅዎ ተገቢ ጭምብል መያዛችሁን ያረጋግጡ።
- እርስዎ /ልጅዎ ማረጋገጥ ያለባችሁ፤
  - ✓ COVID-19 ካለው ማንኛውም ሰው ጋር በቅርብ አለመገናኘታችሁን::
  - ✓ የ COVID-19 ምልክቶች አለመኖሩን (ለምሳሌ ሳል ፣ ትኩሳት ወይም የትንፋሽ እጥረት) ።
  - ✓ ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ ለ COVID-19 ምርመራ አድርገዉ ፖዘቲቭ አለመሆንዎን።
  - ✓ ከፍተኛ ተጋላጭነት ባለበት አካባቢ በመጓዝ ምክንያት ለብቻችሁ እንዲትገለሉ አለመጠየቃችሁን

*የመድረሻዎ ሂደቶች*

ወደ ማእከሉ ሲደርሱ እርስዎ እና ልጅዎ፣

- የ Walker Jones ትምህርታዊ ካምፓስ የፒርስ ጎዳና መግቢያ ይጠቀሙ።
- ከቀጠሮዎ ሰዓት በፊት ከ 5 ደቂቃ በላይ ቀድመዉ አይምጡ።
- የሙቀት እና የጤና ምርመራ ያድርጉ ።
- አስፈላጊ ከሆነ ጭምብል ይዉሰዱ።
- ወደ 3 ኛ ፎቅ የሚሄደውን ሊፍት ይውሰዱ፤ ከዝያ ሰራተኞች ወደ ግምገማ/ምዘና ክፍል ይመሩዋችኋል

*በቀጠሮዎ ወቅት*

በቀጠሮዎ ወቅት እርስዎ እና ልጅዎ ፣

- ወደ ግምገማ ቦታ ከመግባትዎ በፊት የእጅ መታጠብያ ሳንታይዘር ይጠቀሙ።
- ከሌሎች ግለሰቦች ሁሉ በ 6 ጫማ ርቀት ይሁኑ ።
- የፊት ጭምብል ማድረጉን ይቀጥሉ ።
- አለመብላት ወይም አለመጠጣት ።

*መቼ ቀጠሮ ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍ እንደሚቻል*

ከሚከተሉት ውስጥ ማናቸውም ተግባራዊ ከሆነ እባክዎ ቀጠሮዎን ለሌላ ጊዜ ለማስተላለፍ ይደውሉ

- የ 1 አዋቂ እና 1 ልጅ ገደቡን ማሟላት ካልቻሉ።
- እርስዎና ወይም ልጅዎ
  - ✓ COVID-19 ካለው ማንኛውም ሰው ጋር በቅርብ ተገናኝተዉ ከሆነ።
  - ✓ የ COVID-19 ምልክቶች ካለቦት (ለምሳሌ ሳል ፣ ትኩሳት ወይም የትንፋሽ እጥረት) ።
  - ✓ ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ ለ COVID-19 ምርመራ አድርገዉ ፖዘቲቭ ከሆኑ።
  - ✓ ከፍተኛ ተጋላጭነት ባለበት አካባቢ በመጓዝ ምክንያት ለብቻቸዉ እንዲትገለሉ ተጠይቃችሁ ከሆነ።

Walker Jones Education Campus
1125 New Jersey Avenue, NW
Washington, DC 20001

DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

P: 202-698-8037
F: 202-535-1008
www.earlystagesdc.org